# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
## የጉምሩክ ኮሚሽን
# THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
## CUSTOMS COMMISSION


ቀን ኅዳር 03 2012
Date
ቁጥር 4/0314/12
Ref.No.

በአባሪው ለተዘረዘሩት በሙሉ

<u>በያሉበት፣</u>

ጉዳዩ ፡- **<u>የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርዓት ላይ ላጋጠሙ ችግሮች የተሰጠ ውሳኔ ስለማሳወቅ</u>**

የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርዓት ተጠቃሚ ድርጅቶች በአዋጅ ቁጥር 768/2004 እና አዋጁን ተከትለው የወጡ መመሪያዎች መሰረት በተሰጣቸው መብት በመጠቀም ለወጪ ንግድ የሚውሉትን ዕቃዎች ለማምረት የሚያገለግሉ ጥሬ ዕቃዎች፣ አክሰሰሪዎች፣ ማሽነሪዎችና መጠቅለያዎች አስገብተው የሚጠቀሙበት ቢሆንም የስርዓቱ ተጠቃሚዎች የህግ ማዕቀፉን በተገቢው ባለመረዳትና ባለመገንዘብ እንዲሁም በተለያዩ ሌሎች ምክንያቶች በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ቀርበው የማወራረድ ሥራ መስራት ባለመቻላቸው በቅርጫፍ ጽ/ቤቱ አገልግሎትና ውሳኔ አሰጣጥ ላይ አሉታዊ ጫና እየፈጠረ የሚገኝ መሆኑን ጠቅሶ የመፍተሔ አቅጣጫ እንዲሰጠበት በማለት የአ.አ. ቃሊቲ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት በቁጥር 01/ደ43/685 በቀን 13/09/2011 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ጠይቋል፡፡

በመሆኑም የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርዓት የህግ ማዕቀፎችና አሰራሮች በማሻሻል በስርዓቱ ላይ የሚያጋጠሙ ችግሮች ከስር መሰረቱ እስኪወገድ ድረስ የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርዓት አዋጅ ቁጥር 768/2004 እና መመሪያዎቹ አፈፃፀም በባለመብቶቹ በኩል የግንዛቤ እጥረት በመኖሩና መንግስት በወጪ ንግድ የተሰማሩ ድርጅቶችን ለመደገፍ ልዩ ትኩረት አደርጎ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት ለችግሮቹ መፍተሔ መስጠት አስፈልጓል፡፡

ስለሆነም የኮሚሽኑ የበላይ አመራር በቀረቡት ጉዳዮች ላይ ዝርዝር ውይይት በማድረግ ውሳኔ ያስተላለፈ በመሆኑ በውሳኔው መሰረት ተግባራዊ እንዲደረግ የቃለ-ጉባኤውን 04 ገጽ አባሪ አያይዘን የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ደበሌ ቃበታ ሁርሳ
የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር

<u>ግልባጭ፡-</u>

- ለተቋማዊ አቅምና ድጋፍ ዘርፍ
- ለኦፐሬሽን ዘርፍ
- ለህግ ተገዥነት ዘርፍ

<u>ጉምሩክ ኮሚሽን</u>




☎ +251 116 62 98 00
📠 +251 116 62 98 19
✉ 2559
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa,Ethiopia

- ለኤርፖርት ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለቃሊቲ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዳማ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሞጆ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለድሬዳዋ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለባህርዳር ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሐዋሳ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለመቀሌ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅማ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለኮምቦልቻ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅግጅጋ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሚሌ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለሞያሌ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጋላፊ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለጅቡቲ ማስተባበሪያ ቅ/ጽ/ቤት

  <u>በያሉበት</u>፣

1. የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ላይ ያጋጠሙ ችግሮች የሚፈቱበት የውሳኔ ሃሳብ ላይ በተደረገ ውይይት የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርዓት ተጠቃሚ ድርጅቶች በአዋጅ ቁጥር 768/2004 እና አዋጁን ተከትለው የወጡ መመሪያዎች መሰረት በተሰጣቸው መብት በመጠቀም ለወጪ ንግድ የሚውልትን ዕቃዎች ለማምረት የሚያገለግሉ ጥሬ ዕቃዎች፣ አክሴሰሪዎች፣ ማሸጊያዎች እና መጠቅለያዎች አስገብተው የሚጠቀሙበት ቢሆንም የስርዓቱ ተጠቃሚዎች የህግ ማዕቀፉን በተገቢው ባለመረዳትና ባለመገንዘብ እንዲሁም በተለያዩ ሌሎች ምክንያቶች በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ቀርበው የማወራረድ ሥራ መስራት ባለመቻላቸው በቅ/ጽ/ቤቶች እልባት ያላገኙ በእንጥልጥል ላይ ያሉ ጉዳዮች ከመኖራቸው ጋር ተያይዞ የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርዓት የህግ ማዕቀፎችና አሰራሮች በማሻሻል በስርዓቱ ላይ የሚያጋጠሙ ችግሮች ከስር መሰረቱ እስኪወገድ ድረስ የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርዓት አዋጅ ቁጥር 768/2004 እና መመሪያዎቹ አፈፃፀም በባለመብቶቹ በኩል የግንዛቤ እጥረት በመኖሩ እና መንግስት ለወጪ ንግድ የተሰማሩ ድርጅቶችን ለመደገፍ ልዩትኩረት አደርጎ እየተንቀሳቀሰ መሆኑን ግምት ውስጥ በማስገባት ለችግሮቹ መፍትሔ መስጠት አስፈልጓል፡፡ በዚሁ መሰረት የኮሚሽኑ የበላይ አመራር በቀረቡት ጉዳዮች ላይ ዝርዝር ውይይት በማድረግ ከዚህ በታች የተመለከተውን ውሳኔ አስተላልፏል፦

1.1. <u>የማራዘሚያ ጥያቄ ሳያቀርቡ አንድ ዓመት ያለፈባቸው ጥሬ እቃዎችን በመጠቀም ምርት አምርተው ወደ ውጭ የላኩ ድርጅቶችን በተመለከተ፣</u>

እነዚህ ድርጅቶች ምንም እንኳ በህጉ መሰረት በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ቀርቦ ባያወራረዱም ጥሬ እቃ አስገብተው ምርት አምርተው ወደ ውጭ ገበያ በመላክ የውጭ ምንዛሪ ያስገኙ በመሆናቸው፤ ጥሬ እቃውን እና ምርቱን ለሌላ አላማ ያላዋሉ በመሆናቸው መንግስትን ያሳጡት ጥቅም ባለመኖሩ ከቀረጥና ታክስ ነፃ መብት ወደ አገር ውስጥ ያስገቡትን ጥሬ ዕቃ በመጠቀም ምርት አምርተው ወደ ውጭ የላኩ ስለመሆኑ ተጣርቶ በህግ የተቀመጠው ጊዜ ያለፈ ቢሆንም የማወራረድ ሥራ እንዲከናወንላቸው እና በቀጣይ ተመሳሳይ ችግር እንዳይፈፀሙ በደብዳቤ እንዲገለጽላቸው፣